# ሰው ምን ይባል?

ቅርሻቱን የሚልስ - ውሻን ለከስካሳ
ዕርግብን መላዕክ - አሞራን ጥንብ አንሳ፤

ትኳንን ደም መጣጭ - አይጥን ሞገደኛ
ፍልፈልን መሰሪ - ዕባብን መርዘኛ
ጅብን ሰገብጋባ - ዝንጀሮን ሼረኛ፤

ቀበሮን - አታላይ
አህያዎችን - ቻይ፤

ጉንዳንን - ጉልበታም
ነቀዝንም - ሆዳም፤

ፈረስን - አጋሰስ
ዔሊን - ድንጋይ በግሩ
ዓሳን - ሞለጭላጫ
ጦጣን - አጭበርባሪ፤

በጎችን - ሞኛሞኝ
አራዊትን - ጨካኝ……

አረመኔነቱን ለአራዊቱ ትቶ
ለርሱ ስም ሳያስቀር
ስሙን ሁሉ ናኝቶ፤
ባንድ ስም ይጠራል፤
ለራሱ ስም አጥቶ
ሁሉም ሰው ነኝ ይላል።
መጋቢት 2004

አብረሃም በየነ

EthioLion.Com

መኖሬ

ደም ለጠማው መሬት ስንቅ እያዘጋጀ
በነበረበት ወቅት ወጣት እየፈጀ፣

አገዛዙን ንቄ ጮራሽ አነውሬ
ሞትን ኑሬው ነበር ስልጣኑን ደፍሬ፣
ግና ጊዜ ወስዶ

እርሱም ያለፈውን ነገር አስታውሶ
በጉልበቴ መድከም ጥቃቴን ተክሶ
ብዕሬን ሲወርሰው፣
ያኔ ነው መኖሬ የሚሞት እንደ ሰው።

መጋቢት 2004

EthioLion.Com